# የታካሚ መብቶችና ሀላፊነቶች

Holy Cross Health ክብራቸውን በጠበቀ መልኩ ለታካሚዎች እንክብካቤ ያደርጋል። ታካሚዎች የህክምና ሁኔታቸውን በመረዳት ስለህክምና እንክብካቤያቸው ውሳኔዎችን ሲያደርጉ እኛ በተሻለ ሁኔታ ህመምተኞችን ልንንከባከብ እንችላለን። ይህ ደግሞ በታካሚዎቻችን፣ በሀኪሞች እና በጤና ባለሙያዎች መካከል ግልፅነት፣ መተማመንና መከባበርን ይፈልጋል። የሚከተሉት የታካሚ መብቶች ታካሚዎች በ Holy Cross Health ህክምናን በሚያገኙበት ወቅት ምንን ለማግኘት መጠበቅ እንደሚችሉ ይገልፃል። የታካሚዎች ሀላፊነቶች ታካሚዎች በ Holy Cross Health አገልግሎት በሚያገኙበት ወቅት እንዴት መሳተፍ እንዳለባቸው ይገልፃል። የእኛ የትብብር አሰራር ለእያንዳንዱ ታካሚ ደህንነትና ጥቅም የተሻለ ውሳኔን ለማድረግ አስተዋፅኦ ያደርጋል። Holy Cross Health እነዚህን መብቶችና ሀላፊነቶች ህግና የታካሚው ሁኔታ በፈቀደው መሰረት ለታካሚ የጤና ተወካይ ወይም በበጎ ፈቃድ ውሳኔ ሰጪዎችን ያስተላልፋል።

## የታካሚ መብቶች

እርስዎ ያለዎት መበቶች:

1. የሚያስተማምን ህክምናና ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢ የመንፈስና አካላዊ ጤንነትዎን ያነቃቃል።

2. የግል ግላዊነት እና ታሳቢነት፣ ርህራሄ እና አክብሮት የተሞላበት እንክብካቤ። እርስዎን እናዳምጣለን እናም የግል እምነቶችዎን ፣ እሴቶችዎን እና ምኞቶችዎን እናከብራለን። እምነትዎ በሌሎች ደህንነት ጣልቃ እስካልገባ ወይም በሂደት በራስዎ ህክምና ወይም በሀኪምዎ እቅድ ላይ ተፅዕኖ እስካላሳደረ ጊዜ ድረስ ማካሄድ ይችላሉ።

3. ሆስፒታል በሚቆዩበት ወቅት የስነ-ልቦና ድጋፍ እንዲያደርግልዎት የመረጡት ሰው አብሮዎት እንዲሆኑ፣ እንዲጎበኙህ፡ ለምሳሌ ባለቤትዎን፣ የትዳር አጋርዎ (ተመሳሳይ ፆታ የትዳር አጋርን ጨምሮ) ሌሎች የቤተሰብ አባላት፤ ወይም ጓደኛ ሊሆን ይችላል። ሆኖም ግን ማን ሊጎበኝህ በተመለከተ ምንም ጊዜ ሀሳብዎን ለመቀየር መብት አልዎት። ጠያቂዎች በሌላኛው ወገን መብቶች፤ የታካሚው ደህንነት ወይም የመድሃኒት ወይም የህክምና ሂደት ካልተቃረነ በስተቀር አይከለከሉም።

4. ማንኛውም ድንገተኛ ያልሆነ እንክብካቤ ከመሰጠቱ በፊት በእንክብካቤ ዕቅድዎ ልማት ውስጥ ይሳተፉ እና የእንክብካቤ ጥቅማጥቅሞችን እና አደጋዎችን፣ የእንክብካቤ አማራጮቹን እና የእንክብካቤ አማራጮቹን ጥቅሞች እና አደጋዎች ጨምሮ በመረጃ ላይ የተመሠረተ ስምምነት ይስጡ። ህክምናዎን በተመለከተ በማስረጃ ላይ የተመረኮዘ ውሳኔ እንዲያደርጉ እንዲረዳዎት መረጃን እናቀርብልዎታለን። ይህ መረጃ የእርስዎን የጤና ሁኔታ፣ ቅድመ ግምት፣ የምርመራ ውጤቶች፣ የሕክምና አማራጮች እና ተዛማጅ አደጋዎችን እና ሊወስዷቸው ስለሚችሏቸው የአሠራር ሂደቶች ማብራሪያዎችን ሊያካትት ይችላል። የህክምና ውጤትዎ ከእቅድ ውጭ ቢሆንም እንዲያውቁት ሊደረግ ይችላል፡ ፡

5. ስለ ማንኛውም እያከምዎት ስላለ ባለሙያ ስም፣ ደረጃ እና የስልጠና ሁኔታዎች።

6. የትርጉም አገልግሎቶች ወይም የግንኙነት ድጋፍ ያለክፍያ። የትርጉም አገልግሎቶችን በማግኘት ስለ ህክምና ክብካቤና የህክመና እቅዶችን በተመለከተ ከኢንግሊዝኛ ውጭ በሌላ ቋንቋ መረዳት ይችላሉ። የመስማት፣ የንግግር ወይም የማየት ችግር ካለብዎ መግባባትን የሚያመቻቹ የእርዳታ መሳሪያዎችም ይኖሩዎታል።

7. የህክምና ክብካቤዎን በማይጎዳ መንገድ ህጉ በሚፈቅው መሰረት ህክምና (የህክምና ምርምር ጥናቶችን ጨምሮ) ይስማሙ ወይም ይቃወሙ። በህጉ የሚፈቀድ እስከሆነ ድረስ ያለሀኪምዎ ምክር ከሆስፒታል መውጣት ይችላሉ። ካለሀኪምዎ ምክር ከሆስፒታል የወጡ ከሆነ፡ ወይም የህክምና ክብካቤ እቅዱን ካልተከተሉ፤ ለሚደርስብዎት ለማንኛው ጉዳት ወይም ድርግትዎ ለሚያሰከትልብዎች ማንኛውም የገንዘብ እዳ ሆሲፒታሉም ሆነ ሀኪምዎ ተጠያቂ አይሆኑም።

8. የህክምና ክብካቤ ውሳኔዎችን እንዳያደርጉ እንዳይችሉ ሊያደርጉኝ ይችላሉ ብለው የሚያሰባቸውን የሚኞት አቅጣጫዎችን በቅድሚያ ያዘጋጁ። (Holy Cross Health የናሙና ቅፆችን ሊያቀርብልዎ ይችላል።) በእርስዎ ፈንታ

እርስዎን በመወከል ውሳኔዎችን የሚያደርግልዎን ሰው መወከል ይችላሉ። የእርስዎ መመሪያ ህግ፤ እና የሆስፒታሉን ተልዕኮና ፍልስፍና እስካልጣሰ ድረስ Holy Cross Health ይቀበለዋል።

9. የህመም ምርመራ፣ ድጋሚ ምርመራና አያያዝ።

10. ለደህንነት አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር ወይም ለሕክምና አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ከአካላዊ እና ኬሚካዊ እገዳዎች ነፃ መሆን እና ማግለል።

11. የቃል፣ የአእምሮ፣ የአካል እና የጾታ ጥቃትን ጨምሮ ከማንኛውም ዓይነት በደሎች፣ ማግለሎች እና ትንኮሳዎች ነፃ መሆን። እኛ እድሜ፣ ዘር፣ ጎሳ፣ ሀይማኖት፣ ባህል፣ ቋንቋ፣ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳትን፣ የማህበራዊ-ኢኮኖሚ ሁኔታዎች፣ ፆታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም አገላለፅን፣ ወይም ለህክምናዎ የክፊያ ምንጭን መሰረት በማድረግ ምንም አይነት ልዩነት አናደርግም።

12. የ HIPAA Notice of Privacy አሰራርን ግልባጭ ማግኘት።

13. ተቀባይነት ባለው ጊዜ ውስጥ የህክምና ማህደርዎን ማግኘት። በጤና ክብካቤ ውይይት፣ በህክም እና ስለ ጤናዎ አመዘጋገብ ወቅት ብቸኝነት እና ሚስጢረኝነትን መጠበቅ ይችላሉ። ሆስፒታሉ የታካሚዎችን መረጃ በህክምና ክብካቤ ለሚሳተፉ ወይም ሌሎች መረጃውን ለማግኘት ህጋዊ መብት ላላቸው በስተቀር አያሳይም። እርስዎ ወይም ህጋዊ ተወካይዎ የህክምና መረጃ ግልባጩን በነፃ ማግኘት ይችላሉ። ግልባጩን ለማግኘት Holy Cross Health የህክምና ማስረጃዎች ክፍልን (Medical Records department) በፅሁፍ መጠየቅ ይችላሉ።

14. ከአስቸኳይ ጊዜ የህክምና እና ለምጥ የህክምና ምርመራ ያድርጉና የማስታገሻ ህክምናን ያግኙ። የሚቀበሉዎትን ሀኪምና ሆስፒታል በመጠየቀ ካረጋገጡ በኋላ የህክምና ክትትሎዎን ወደ ሌላ ሀኪም እና/ወይም ተቋም ሊያስተላልፉ ይችላሉ። የጠየቁት የህክምና አገልግሎት በ Holy Cross Health የማይሰጥዎት ከሆነ በየትኛውም ጊዜ የህክምና ክትክሎዎን ወደ ሌላ ሊያስተላልፉ ይችላሉ። ሆስፒታሉ በችሎታ ማነስ ወይም ተልዕኮውን ወይም ፍልስፍናውን የሚቃረን ከሆነ አገልግሎት ላይሰጥ ይችላል። በእነዚህ ሁኔታዎች ታካሚው ወደ ሌላ የተጠየቀውን አግልግሎት ሊሰጥ ወደሚችል የህክምና ተቋም ለማስተላለፍ አስፈላጊ ጥረቶች ይደረጋሉ። ሆስፒታሉም ለእርስዎ ወይም ለጤና ክብካቤ ተወካይ ወይም ለበጎፈቃድ ውሳኔ ሰጪ አካል ለምን ማስተላለፉ እንዳስፈለገና ስለሌሎች አማራጮችን አስመልክቶ ያብራራል። ማስተላለፉም በአንተ ወይም በጤና ክብካቤ ተወካይ ወይም በበጎፈቃድ ውሳኔ ሰጪ አካል እውቅና እና ለህክምና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ብቻ የሚከናወን ይሆናል።

15. ሆስፒታሉ ከሌሎች የጤና መስጫ እና የትምህርት ተቋማት ጋር ስላለው ግንኙነት በተመለከተ መረጃ።

16. ከህክምና አላማ ውጪ ፎቶዎን ለመስጠት መፍቀድ ወይም መከልከል።

17. ከሆስፒታሉ ስለመውጫ እቅድና ለአንተ ህክምና የተለዩ ተገቢ አማራጮችን በመለከተ ተሳተፍ።

18. ስለሆስፒታሉ እና የሀኪሙ ክፍያ በተመለከተ መረጃ ይቀበሉ። አገልግሎቱ እስካልተከለከለ ድረስ የጤማ ክብካቤውን ከመጀመሩ በፊት አሰቀድመው ስለሆስፒታሉ ዋጋ ግምት ይወቁ። ከጠየቁ ስለሆስፒታሉ ክፍያ፣ ክፍያውን ለመፈፀም እንዴት እርዳታ እንደሚያገኙ፣ ወይም የዋስትና ቅፅን በመሙላት በ Holy Cross Health የታካሚዎች የሂሳብ ክፍል በኩል እንዴት እርዳታ ማግኘት እንደሚቻል አስመልክቶ መረጃ ያገኛሉ።

19. ማንኛውም ጥያቄ ቢኖርዎት ወይም የሚያሳስብዎት ነገር ቢኖር ስለሆስፒታሉ ፖሊሲዎች መግለጫ ቢያስፈልግዎ ወይም ሌላ የተለየ ፍላጎት ቢኖርዎ የክፍሉ የነርስ ዳሬክተር/ የነርስ መሪን ያነጋግሩ። ከመረጡም የታካሚ እና ቤተሰብ ግንኙነቶች ክፍልን ማነጋገር ይችላሉ። 301-754-7495 በ Holy Cross ሆስፒታል ወይም 301-557-6495 በ Holy Cross Germantown ሆስፒታል.

20. በርስዎ እንክብካቤ የማይስማሙ ወይም የሚያሳስቡዎት ጉዳዮች ካሉ አቤቱታ/ቅሬታ እንክብካቤዎን ሳይነካ የቃል ወይም የጽሑፍ አቤቱታ/ቅሬታ ለሆስፒታሉ የሕመምተኛ እና የቤተሰብ ግንኙነት መምሪያ ያቅርቡ። የእኛ የቅሬታ ሂደት

ለእርስዎ ብዙውን ጊዜ በሰባት ቀናት ውስጥ ለጤና እንክብካቤ ወኪልዎ ወይም ተተኪ ውሳኔ ሰጪ በወቅቱ ምላሽ የመስጠት መብት ያቀርባል። ይህም በታካሚው ፋንታ የቀረበውን ቅሬታ ለማጣራት የሚወሰዱ እርምጃዎችን፣ ማንኛውም የማጣራት ስራ ውጤቶች፣ የማቢቂያው ቀን እና በሆስፒታሉ ማነጋገር የሚቻል ሰው አድራሻ የሚያካትት ይሆናል።

21. የተከላካይና የጥብቅና አገልግሎቶች ዝርዝር መቅረብ። እርስዎ፣ የጤና ተወካይዎ ወይም የበጎ ፈቃድ ውሳኔ ሰጪ የሆነ ሰው የታካሚውን እንክብካቤ በተመለከተ ማንኛውን ቅሬታ እና/ወይም በሆስፒታሉ ውስጥ ያልተመለሱ የደህንነት ስጋት ካላችሁ የሚከተሉትን ተቋማት ያነጋግሩ፡

The Joint Commission
One Renaissance Blvd, Oakbrook Terrace, Illinois 60181
ስልክ: 1-800-994-6610 | ፋክስ: 630-792-5636
ኢሜይል: patientsafetyreport@jointcommission.org

Maryland Department of Health and Mental Hygiene,
Office of Health Care Quality
7120 Samuel Morse Dr, 2nd Fl, Columbia, Maryland 21046
ስልክ: 410-402-8000 | www.health.maryland.gov/ohcq

Maryland Board of Pharmacy, Maryland Department of
Health and Mental Hygiene
4201 Patterson Ave, Baltimore, MD 21215
ስልክ: 410-764-4755 | TTY: 1-800-735-2258
ፋክስ: 410-358-6207 | ኢሜይል: Dhmh.mdbop@maryland.gov
www.health.maryland.gov/pharmacy

The CMS Quality Improvement Organization for Maryland
LIVANTA LLC
BFCC-QIO
10820 Guilford Rd, Ste 202, Annapolis Junction, MD 20701-1105
ስልክ: 888-396-4646 | TTY: 888-985-2660
Office for Civil Rights Mid-Atlantic Region – DE, DC, MD,
PA, VA, WV

U.S. Department of Health and Human Services
150 S. Independence Mall West, Suite 372, Public Ledger
Building, Philadelphia, PA 19106-9111
የደንበኛ ምላሽ ማዕከል: 800–368–1019 | TDD:
ፋክስ: 202-619-3818 or 215-861-4431 | TDD: 800-537-7697
ኢሜይል: ocrmail@hhs.gov

Holy Cross Health Ethics Advisory Committee
ስልክ: 301-754-7024

## የታካሚ ሀላፊነቶች

እርስዎ ያለዎት መብቶች:

1. በተቻለዎት መጠን ትክክለኛ የህክምና ታሪክዎን ማቅረብ። ስላለፉት ህመም ሁኔታ፣ ሆስፒታል ተኝተው የታከሙበትን፣ መድሃኒቶችና ሌሎት ከርስዎ ጤና ጋር የሚገናኙ መረጃዎችን ሊጠየቁ ይችላሉ።

2. በሆስፒታል ውስጥ ባሉበት ወቅት ለቀጥተኛ ወይም የተወሰነ ህክምና ለበጎ ፈቃድ ውሳኔ ሰጪን ወይም ለእርስዎ ህክምና ተጠያቂ ለሆኑ ግለሰቦች የበፊት መመሪያ ግልባጮችን ወይም ሌሎች ሰነዶችን ያቅርቡ። ምንም አይንት የበፊት መመሪያ ግልባጮች ከሌለዎት ስለ ህክምና ፍላጎትዎ እቅድ እና የህክምና አያያዝ በተመለከተ ለህክምና አቅራብህ መንገር ያንተ ሀላፊነት ነው።

3. ሆስፒታል ውስጥ በሚቆዩበት ወቅት ለግል ንብረትዎና ሃብትዎ ሀላፊ ይሁኑ።

4. ተገቢ ያልሆኑ ህክምናዎችን፣ አግልግሎቶችንና ክብካቤዎችን አለመፈለግ።

5. ከርስዎ የጤና ክብካቤ ቡድን ጋር በትክክል መነጋገርና መተባበር። ይህም ሁሉንም የቡድኑ አባላት ተገቢውን የህክምናዎ ግብ ለማሳካት እንዲሰሩ ያስችላል።

6. ሌሎች ታካሚዎችንም ከግንዛቤ ውስጥ ያስገቡ ይሁኑ። ጠያቂዎትም ሌሎችን ከግንዛቤ ውስጥ ያስገቡ መሆናቸውን ያረጋግጡ።

7. ቀጠሮዎን ይጠብቁ። የቀጠሮዎን ሰዓት መጠበቅ ካልቻሉ በሆስፒታሉ ለሚመለከተው ክፍል ይደውሉ።

8. ለሌሎች እና ለሆስፒታሉ ንብረቶች ክብር ያለዎት ይሁኑ።

9. የትኛውም መብትዎ የተነካ ወይም ሊነካ እንደሆነ ካሙኑ በተቻለ ፍጥነት በቶሎ ለ Holy Cross Health ያስውቁ። ይህንንም ለታካሚ እና ቤተሰብ ግንኙነቶች በ 301-754-7495 ላይ ለ Holy Cross ሆስፒታል ወይም በ301-557-6495 ላይ ለ Holy Cross Germantown ሆስፒታል በየትኛውም ጊዜ መደወል ያችላሉ። ከመደበኛው የስራ ሰዓት ውጪ ከሆስፒታሉ ተወካዮች ጋር ለማውራት ለስልክ ተቀባይ በ 301-754-7000 ላይ ለ Holy Cross ሆስፒታል ወይም 301-557-6000 ላይ ለ Holy Cross Germantown ሆስፒታል በመደወል የአስተዳደር አስተባባሪውን ለማናገር ይጠይቁ።